# አሮጌው በር






በስመ አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን።

"ንዌጥን በረድኤተ እግዚአብሔር"

# አሮጌውን በር እናድስ!

*መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።*

እንግዲህ....

**እንግዲህ አሮጌውን በራችንን እናድስ ስንል የቀደመውን የእግዚአብሔርን Principles እንደ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ሃሳብ እንወቃቸው እያልን ነው።**



"We have to rest upon old principles of God, these truths will never change."

[R. Stedman]

† እግዚአብሔር ሰዉን በዓርአያዉ በአምሳያዉ ለክብሩ ፈጥሮ፤ ሁሉንም ከእግሮቹ በታች አስገዝቶ፤ በገነትም አኑሮት ነበር። ገና በጥዋቱ በሴይጣን ተንኮል ተታሎ ከበደለዉ በኋላ፥ አስቀድሞ እንደነገረዉ ክብሩን ገፎ፤ እንደሚያድነዉ ግን ተስፋ ሰጥቶ ከገነት አዉጥቶታል።[ዘፍ3[15]]

† አዳምና ሔይዋንም ከገነት ሲወጡ እግዚአብሔር አምላክ ለሰዉ ዘር የገባዉን ተስፋ እዛዉ በራሳቸዉ ዕድሜ ያገኙ መስሏቸዉ ከጅምሩ "ወንድ ልጅ ከእግዚአብሔር አገኘን" ሲሉ "ቃየን" ብለዉ ጠርተዉት ነበር። ።[ዘፍ4[1]]



† ቃየን ግን ሞቶላቸዉ የሚያሳርፋቸዉ ሳይሆን፤ የገዛ ወንድሙን ሳይቀር የሚገድል ነፍሰ ገዳይ ኃጢአተኛ ሆኖባቸዉ፤ ሴት እስከተወለደበት ድረስ ለሁለት መቶ ዓመታት ያህል ተስፋቸዉን ቀብሮባቸዋል።[ዘፍ5[3]]

† አዳምም እንዳሰበዉ የመዳኑን ቀን በሕይወት ዘመኑ ሳያይ ሞተ፤ ምንም ሰዉ በምድር ላይ እየበዛ ቢመጣም ከእግዚአብሔር ጋር የነበረዉ ግንኙነት ግን እጅግ እየተበላሸ፤ እንደዉም በሰዉ ቋንቋ እግዚአብሔር ሰዉን በመፍጠሬ ተፀፀትኩ እስኪልና ከተመረጠዉ ከሴም ወገን ጻድቁን ኖኅና ቤተሰቡን ብቻ አስቀርቶ የፈላ ዉሃ አዉርዶ እስኪያጠፋዉ የሄደ ነበር።



† በዚህ ሁሉ የሰዉ ልጅ ዉድቀት፥ ከጎሰቆለዉ ባህርይዉ በለፈ የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ ለማሰናከል ቆርጦ የተነሳዉ የቀደመ ጠላቱ ሴይጣንም ስለነበረበት፤ እግዚአብሔር ከተመረጠዉ የሴት ነገድ የሚመጣዉን አዳኝ መምጫ ከሴይጣን በመሰወር፤

- ከሴት ነገድ አብርሃምን፤
  - ከአብርሃም ይስሃቅን፤
    - ከይስሃቅ ያዕቆብን፤
      - ከያዕቆብ አስራ ሁለቱን ነገድ፤
        - በአስራ ሁለቱ ነገድ ደግሞ ለሁለት ዓላማዎች እስራኤልን መስርቷል።



† እስራኤል የተመሰረተችበት/የተመረጠችበት ዓላማዎች፡-

1. የሰዉ ዘር በሙሉ የፈጠረዉ ፤ አሁንም የሚሠራ አምላክ እንዳለ እንዲያዉቅ ሕያዉ ምስክር እንድትሆን፤

1. የሰዉን ዘር በሙሉ የሚቤዠዉ መድህን የሚመጣባት ትዉልድ ስለሆነች።

† አመሰራረቷም፡

- ዮሴፍ ወደ ግብፅ ተሸጦ በዚያ ነገሰ፥
- ያዕቆብም በምግብ እጦት ሰባ ነፍስ ሆኖ ግብፅ ወረደ፥
- ከ430 ዓመታት በኋላ ባህር ከፍሎ በማሻገር እራሱ እስራኤልን መሰረታት፥
- 40 ዓመታት በምድረበዳ መራቸዉ፤ ኋላም የማለላቸዉን ምድር አወረሳቸዉ፥
- ወደ 300 ዓመታት በመሳፍንቶች መራቸዉ፥
- ንጉስ ይንገስልን ባሉት መሠረትም ሳዖልን፥ ዳዊትን፥ ሰሎሞንንም አነገሰላቸዉ፥
- በሰሎሞን ልጅ በሮብአም ዘመን ግን እስራኤል ለሁለት ተከፈለች፥ የእስራኤል እና የይሁዳ መንግስት በመባል፥
- የሰሜኑን እስራኤል መንግስት ወደ 700 (722) ዓ.ዓ አከባቢ አሶራዊያን ማረኳቸዉ፥
- የደቡቡ ይሁዳ መንግስትም ወደ 605(607) ዓ.ዓ አካባቢ በባቢሎናዊያን ተማረከ።

† የባቢሎኑ ንጉስ ናቡከደነፆር፡-

- ኢየሩሳሌምን መቅደሱንም በማፍረስ ከእግዚአብሔር ቤት ዕቃ አያሌዉን ወደ ባቢሎን አፍልሶ በራሱ መቅደስ አኑሯል። [2ዜና36 5-8]
- ሕዝቡንም የተስፋ ምድሩ ላይ እንዳይቀመጥ አፍልሶታል። መልካሞቹን፥ ጥበብም፥ ብልሃትም፥ ማስተዋልም የሞላባቸውን የከለዳውያንን ቋንቋና ትምህርት አስተምሮ በመንግስቱ ሾሟቸዋል።[ዳን1 1-7]
- ዳንኤል፥ ኤርምያስ፥ ሕዝቅኤል፥ አናንያ፥ አዛርያ፥ ሚሳኤልም በዚሁ ጊዜ የነበሩ የእግዚአብሔር ሰዎች ነበሩ።



† ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቀጠረለት 70ዉ የምርኮ ዘመን ሲያበቃ፥ በሦስት ዙር ተመልሰዋል።

1ኛ) በዘሩባቤል መሪነት፡- በ537 ዓ.ዓ

2ኛ) በዕዝራ መሪነት፡- በ458 ዓ.ዓ

3ኛ) በነህምያ መሪነት፡- በ445 ዓ.ዓ ናቸዉ።

† በተለይ ነህምያ ሲመለስ የኢየሩሳሌምን ቅጥር የመስራት ራዕይ ይዞ ስለነበረ፤ አስቀድሞ በመፆም በመፀለይም ከንጉሱ ዘንድ ለሥራው የሚያስፈልገውን ሁሉ የሚያስቀርብ ደብዳቤ በመቀበል፤ ወደ ኢየሩሳሌም በመምጣት የቅጥሩንም ሁኔታ በማየት፤ “እኛ ያለንበትን ጕስቍልና ኢየሩሳሌም እንደ ፈረሰች፥ በሮችዋም በእሳት እንደ ተቃጠሉ ታያላችሁ አሁንም ከእንግዲህ ወዲህ መሳለቂያ እንዳንሆን ኑና የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንሥራ ” ብሎ ሕዝቡን በማነሳሳት የቅጥር ስራውን በ52 ቀናት አጠናቋል።



ማስታወሻ

† በቀደመዉ ዘመን ቅጥር የሉአላዊነት መገለጫ ነዉ። ከጠላቶቻቸዉ ለመከላከልም ከተማቸዉን እጅግ ወፍራም እና ረጅም ቅጥር ይከልሉ፤ መግቢያ መዉጫ በርም ያደርጉበት ነበር። (ለምሳሌ የኢያሪኮ ቅጥር 90ሜ ስፋት 45ሜ ቁመት ነበረዉ)። ኢየሩሳሌምም እንዲሁ የተቀጠረች፥ አሥርም በሮች የነበሯት ከተማ ነበረች።

† በነህምያ የተመራዉን የኢየሩሳሌም ቅጥር ሥራ ከጥቂቶች በቀር፤ ሁሉም ተሳትፈዉ ሲሰሩት፤ አስሩ የኢየሩሳሌም በሮችም ታድሰዋል። አስቀድሞ የበግ በር፥ ቀጥሎም የዓሳ በር፥ ቀጥሎም አሮጌው በር፥ እንዲሁ የሸለቆው በር፥የጕድፍ መጣያውም በር፥ የምንጩም በር፥ የውሃውም በር፥ የፈረሱም በር፥ የምስራቁም በር፥ በመጨረሻም የሐሚ ፍቃድ (የፍርድ)በር እስከበጉ በር ታድሷል።

† በዚህም የኢየሩሳሌም ቅጥር መታደስ፤ ናቡከደነፆር ያፈረሳት ሀገርና ከተማ ወደቀደመዉ ሉአላዊነቷ መመለሷን ያመለክታል!!





## ሚስጢሩ

† እስራኤል እጅግ ለተለየ ዓላማ መመስረትዋን ካወቅን፤ ኢየራሳሌምም የታላቁ ንጉሱ ከተማነቷ ከገባን (ማቴ5[35])፤ **ቅጥሯም ይሁን በሮቿ፥ የበሮቿም ቁጥር ይሁን የበሮቿ ስሞች እንዲሁ እንዳልተሰጣቸዉ ይገባናል።**

† ስለዚህም የኢየራሳሌም ቅጥሯ፥ በሮቿ፥ የበሮቿ ቁጥርም ስምም ልዩ መንፈሳዊ ትርጉም አላቸዉ።

መጽሓፍ ቅዱስ፡-

"ቅጥር እንደሌላት እንደ ፈረሰች ከተማ፥

መንፈሱን የማይከለክል ሰው እንዲሁ ነው።"

ምሳ25[28]



## ሚስጢሩ.....

- ቅጥር የመንፈሳዊ ሕይወት፥
- በሮቿና ስሞቿ የመንፈሳዊ ሕይወት መርሆቻችን(ፕሪንስፐስ)፥
- ቅጥር የሌላት ከተማ ሉአላዊነት እንደሌላት ፤እግዚአብሔር መር ያልሆነ መንፈስም ሕይወት የለዉምና፥
- በሮቹ አስር መሆናቸዉ የፍጹምነት ምሳሌ!



## ሚስጢሩ

- ነህምያ በእግዚአብሔር አንዲያ ልጅ የሚያምን ምዕመን፥
  - ቅጥር የመንፈሳዊ ሕይወቱ፥
    - በሮቿና ስሞቿ የመንፈሳዊ ሕይወቱ መርሆች፥
  - በሮቹ አስር መሆናቸዉ ወደ ፍጹምነት የማምራቱ፥
- መታደሱ በበጉ በር ተጀምሮ በበጉ በር መፈጸሙ፤ የጌታ መስቀልና መሞት የነገር ሁሉ ቁልፍ የመሆኑ ምሳሌ!



የኢየሩሳሌም ቅጥሯም ይሁን በሮቿ እጅግ ልዩ መንፈሳዊ ትርጉም እንዳላቸው፤ ነህምያም እያንዳንዳችንን በጌታ ያመንን እኛን የሚወክል ሲሆን፤ ቅጥሩ ክርስቲያናዊ ሕይወታችን፤ በሮቹም የሚወጣውን የምናስወጣበት ፣ የሚገባውን የምናስገባበት እና ሁሌም የምናድሳቸው/የምንታደስባቸዉ መንፈሳዊ የእግዚአብሔር መርሆች እንደሆኑ እንገነዘባለን።

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

ማስገንዘቢያዎች

† የኢየሩሳሌም ቅጥሯና በሮቿ የታደሰዉ አስቀድሞ በዘሩባቤል የአምልኮ ማዕከል የሆነው ሁለተኛው ቤተመቅደስ ከተሰራ እና የክህነቱ ስርዓት በዕዝራ ከተጠናከረ በኋላ መሆኑ፤

በእግዚአብሔር ቤተመቅደስ የተመሰለዉ፥ የሰዉ ልጅ ድነቱና የመንፈሱ ማደሪያ መሆኑ ከተፈጸመ በኋላ፤ ምህረትን በማግኘት ከጨለማ ወደ ሚደነቅ ብርሃን በተጠራበት መጠራት የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህን፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን መሆኑ ከተጠናቀቀ በኋላ፤ ቀጣዩ ምዕራፍ ቅጥሩን መጠገን፥ በሮቹንም ማደስ ሆኖ እናገኘዋለን። ይኸውም ከድነት በኋላ ያለዉ ክርስቲያናዊ የቅድስና ጉዞዉ ማለት እንደሆነ ይገባናል።

† አንድም የቤተመቅደሱ መሰራት፡- ከእግዚአብሔር መወለዳችን የመንፈሱም ማደሪያ መሆናችን (ጌታን መቀበላችን)፤ ኢየሩሳሌም፡- እያንዳዳችን በጌታ ያመንን፤ የኢየሩሳሌም ቅጥር፡- የክርስትና ሕይወታችን፤ በሮቿም፡- ክርስቲያናዊ እግዚአብሔራዊ መርሆቻችን።

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

ስለዚህም…

አስሩ በሮች የተለየ ሚስጥር፥ እጅግ የተለቀ ትርጉምም እንዳላቸው ይገባናል።

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

1ኛ-የበግ በር (Sheep Gate)[ነህ3[1]]፡-በጎች ወደ ኢየሩሳሌም የሚገቡበት በር ነው። በተለይ ለመሰዋዕት የሚቀርቡት በጎች የሚገቡት በዚህ በር ነው።

- ይህ በር በቀጥታ የዓለምን ኃጢአት ያስተሰረየውን አማናዊ በግ ጌታችን አምላካችንም ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ በኩል ያደረገውን መስዋትነቱን ያመለክታል።
- በዚህም የበግ በር "principle of the cross" ነው። ይኸውም የራሳችንን ፕላን እና እኔነታችንን ጥለን የምንሸከመዉን መስቀል፣ የምናገለግለውንም አገልግሎት ያመለክታል።

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

የበጎች በር ጌታ ስለ በግ እረኝነቱ በተናገረበት አንቀጽ "በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፥ ይገባልም ይወጣልም መሰማሪያም ያገኛል።"[ዮሃ10[9]]ያለዉ እንደሆነ እናዉቃለን።

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።






2ኛ-የዓሳ በር (Fish Gate)[ነህ 3[3]]፡- ዓሳ ወደ ኢየሩሳሌም የሚገባበት በር ነው። ጌታ በገሊላ በህር አጠገብ ያገኛቸውን ዓሳ አጥማጆች የነበሩትንም ጴጥሮስና እንድርያስን፤ ዩሃንስንና ያዕቆብንም "በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ።" [ማር1[17]] ባለው አባባሉ ስንመዝነው የዓሳ በር ምስክርነትን (witness) የሚያመልክት ሆኖ እናገኘዋለን።

- ሁሉም ክርስቲያን በሕይወቱም ይሁን በቃሉ ምስክር እንደሆነ ጌታ በማያሻማ ቃል "በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ የሰው ልጅ በክብሩ በአባቱና በቅዱስ መለዕክት ክብርም ሲመጣ በእርሱ ያፍርበታል።"ብሏል። [ሉቃ9[26]]
- የዓሳ በር ለክርስቶስ በሕይወትም ይሁን በቃል የምንሰጠው ምስክርነት የሚያመለክት ስለሆነ ይህን በር ሁሌም ማደስ እንደሚገባ እናያለን። "ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና።" [ሮሜ10[9-10]] እናንተ የምድር ጨው፣ብርሃንም ናችሁ።[ማቴ5[13-16]]



ይህ ትምህርት ቤተክርስቲያን በቃል የምታደርገዉን ምስክርነት ለመደገፍ ነገረ-ድነት ለይ ያነጣጠረ እንደሆነ እዚህ ቦታ ለይ መናገር ይቀለናል!!





3ኛ-አሮጌዉ በር (Old Gate)[ነህ3[6]]፡- እዉነት አሮጌ ነዉ። "truth is always old that everything is rest upon" እንደተባለው። ሁሉም እውነት አሮጌ ነው፤ ሁሉ አዲስ ግን እውነት አይደለም።

"እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ። እውነትም በእርሱ ስለሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና። [ዩሃ 8[44]] ብሎ ጌታ ስለዲያብሎስ ከተናገረው አንቀፅ እንደምንገነዘበው ከመጀመሪያ የነበረው እውነት ነው። እርሱም እግዚአብሔር ነው።

- † እግዚአብሔር እውነት ነው። ሃሰት በርሱ ዘንድ የለም። "እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤" እንዳለ ጌታ በዩሃ14[6]
- † አሮጌው በር የሚያሳየው የቀደመውን የእግዚአብሔርን ፕሪንሲፕልስ ነው። በፍጥረት ሥርዓት አስቀድሞ የዘጋጀውን የሰውልጅ ቢያበላሽም፤ በዉድ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ ቀደመዉ ክብሩ ሲመልስ፥ እርሱ ባለመለወጥ ሰዉን ብቻ ሲለዉጠዉ እናያለን። "እግዚአብሔር አይለወጥምና "[ሚል3[6]]








4ኛ-የሸለቆ በር (Valley Gate)[ነህ3[3]]፡- የቅጥሩ ዝቅተኛ ቦታ ለይ ያለ በር ነዉ። የሚያመለክተዉም Humility and Lonliness of Mind ነዉ።

- የተሰበረ መንፈስ፣ ራስን ዝቅ በማድረግ ሌላው ሰው እንዲሻል መቁጠር (ትህትና) ፤ ከራስ ይልቅ ሌላ ሰው እንዲጠቀም ማስቀደም (የዋህነት)ነዉ። በሌላ ቋንቋ በመንፈስ ድሃ መሆንን ያመለክታል።
- [ማቴ11[29]]"ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና"..አማናዊው መምህረ ትህትና እርሱው ራሱ ነዉ!!!!
- ታላቁ መምህረ ትህትና ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረን፥ ያሳየንም[ዩሃ13[1-20]]፤ እንዲሁም በእኛም እንዲኖሩ የሚፈልገው ብቸኛው ሃሳብ [ፊል2[1-11] ና 2ቆሮ8[9]] የህይወታችን የሸለቆ በር እንዲታደስ ነዉ። ይኸውም በትህትና እንድናመልከው ፥ እንድናገለግለውም ነው።
- [ያዕ4[6]]"እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል"...ጸጋዉን ለትሁታን ብቻ ይሰጣል!!



## መሰረታዊ ጥቅሶች

- [ኢሳ66[2]]"ነገር ግን ወደዚህ ወደ ትሑት፥ መንፈሱም ወደ ተሰበረ፥ በቃሌም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ።"...ዓይኖቹ ወደ ትሁታን ነዉ!
- [መዝ51[16-17]]"መሥዋዕትን ብትወድድስ በሰጠሁህ ነበር የሚቃጠለውም መሥዋዕት ደስ አያሰኝህም። የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው፥ የተሰበርውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም።"
- [ሚክ6[8]] "ሰው ሆይ፥ መልካሙን ነግሮሃል እግዚአብሔርም ከአንተ ዘንድ የሚሻው ምንድር ነው? ፍርድን ታደርግ ዘንድ፥ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ፥ ከአምላክህም ጋር በትሕትና ትሄድ ዘንድ አይደለምን?"
- [ሮሜ12[16]] "እርስ በርሳችሁ በአንድ አሳብ ተስማሙ፤ የትዕቢትን ነገር ኣታስቡ፥ ነገር ግን የትሕትናን ነገር ለመሥራት ትጉ። ልባሞች የሆናችሁ አይምሰላችሁ።"
- [1ጴጥ5[5]] "እንዲሁም፥ ጐበዞች ሆይ፥ ለሽማግሌዎች ተገዙ፤ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፥ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል።"






5ኛ-የጉድፍ መጣያ በር (Dung Gate)[ነህ3[14]]፡- የኢየሩሳሌም ከተማ ቆሻሻ የሚጣልበት በር ነዉ።

ይህ በር በቀጥታ ፍጹም ቅዱስ (Absolutly Holy) በሆነው አምላካችን እግዚአብሔር ፊት ስንቆምም፥ ይሁን ስናገለግለው ጉድፋችንን የምንጥልበትና ከኃጢአታችን የምንነጻበት የንስሓ በር እንደሆነ ይገባናል። ንስሃ ከማይፈልጉ ጻድቃን ይልቅ ቆሻሻምነቱን አውቆ በሚናዝዝ ኃጢአተኛ እግዚአብሔር እጅግ ደስ ይለዋል፤ በመመለሱም በሰማይ መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል።[ሉቃ15[10]]

- † ያለመነ ጌታን በማመን፤ ያመነ ደግሞ ትልቅም ይሁን ትንሽ፥ የቀድሞዉም ይሁን አዲሱ፥ የሚመራም ይሁን የሚመራ፥ የሚሰብክም ይሁን የሚሰበክም፥ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያመነ ሁሉ፤ ለጸሎትም ይሁን ለአምልኮ፥ ቃሉን ለመስማትም ይሁን ለማሰማት፥ ለማገልገልም ሲዘጋጅና ሲያገለግል ሁሌም በጉድፍ ማጠቢያ በር መግባት እንዳለበት እናያለን።

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

## ማስገንዘቢያ

- † ምንም እንኳ በጌታ ያመንን ቢሆንም፥ ምንም እንኳ የዘላለምን ሕይወት ያገኘን ቢሆንም መዳናችን የሚፈጸመዉ ክርስቶስን በምንመልስበት በቤዛነታችን ቀን በመሆኑ ዘወትር የጉድፍ ማጠቢያ በራችንን ማደስ እንደሚገባን እንገነዘባለን። በአሁኗ ቅፅበት እንኳ የከበረው የክርስቶስ ደም ሸፍኖን እንጂ በእግዚአብሔር ፊት ጥቁር ኃጢአተኞች ነን።

[1ዮሃ1[7-10]] "ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፥ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል። ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው። ኃጢአትን አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ እናደርገዋለን ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም።"

[1ዮሃ2[1-2] ] "ልጆቼ ሆይ፥ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ። ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱም የኃጢአታችን ማስተስሪያ ነው፥ ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኃጢአት እንጂ።"

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

"God is Absolute Holy and we are Black Sinners!"

..... ወደ ጉድፍ መጣያ በራችን ሁሌም ጎራ ማለት ትህትና ሳይሆን እዉነት እንደሆነ እናያለን !!!

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።






6ኛ-የምንጭ በር (Fountain Gate)[ነህ3[15]]፡- ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ የሚመነጩ ምንጮች የሚገቡበት በር ነዉ። "Holy sprit is the river of life" መንፈስ ቅዱስ የሕይወት ምንጭ ነዉ።

[ዩሃ7[37-39]]"ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ። በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ፥ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ።ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ።"

[ዩሃ4[14]]"እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም፥ እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ አላት።"








7ኛ-የዉሃ በር (Water Gate)[ነህ3[26]]፡- ለኢየሩሳሌም ከተማ ዉሃ የሚገባበት በር ነዉ። ውሃ የእግዚአብሔር ቃል ምሳሌ ነው።

† ይህ በር አልታደሰም። አልፈረሰምና! ይኸውም የእግዚአብሔር ቃል የማይፈርስ፥ የማይታደስ ይልቁንም የሚሰራ፥ የሚያድስ የመሆኑን ምሳሌ።

[መዝ18[30]] "የአምላኬ መንገድ ፍጹም ነው፥ የእግዚአብሔር ቃል የነጠረ ነው፥ በእርሱ ለሚታመኑት ሁሉ ጋሻ ነው።

[መዝ33[4]] "የእግዚአብሔር ቃል ቅን ነውና ሥራውም ሁሉ በእምነት ነውና።"

† ነህምያና ዕዝራ በዚሁ በር አጠገብ ባለው አደባባይ የህጉን ቃል ያነቡ ያስተምሩም ነበር።[ነህ8[3]]






8ኛ-የፈረስ በር (Horse Gate)[ነህ3[28]]፡-ፈረሶች ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ የሚገቡበትና የሚወጡበት በር ነዉ። ተምሳሌነቱ የጦርነት ነው።
[ኤፌ6[10-17]]

† በቅሎና አህያ ለይ መቀመጥ የሰላም ምልክት እንደሆነ ሁሉ፤ እግዚአብሔር የእስራኤልን ነገስታት ፈረስ እንዳያበዙ በከለከላቸዉና ከምናነባቸዉ መጽሓፍ ቅዱሳዊ ጦርነቶች እና ራእዮች የፈረሶችን ጦርነት ተምሳሌነት በግልጽ እንመለከታለን።

በዚህ ዓለም ክርስቲያኖች የኢየሱስ ክርስቶስ ወታደሮች ናቸዉ። ሁሌ ትጸልዩ ዘንድ ትጉ የሚለዉ ትዕዛዝም የሚያሳየዉ ጦርነቱ መንፈሳዊ፥ ዉጊያዉ የማያቋርጥ፥ የዉጊያዉም አምድ ቤተክርስቲያን እንደሆነች እናያለን።



# ክርስቲያን በሦስት “C”ዎች ሲገለጽ:

## CHRSTIAN:

- CONTINOUSLY IN TROUBLE
- COMPLETLY FEARLESS
- CONSTANTLY JOYFUL.



## መሰረታዊ ጥቅሶች

- [ኤፌ6[10-17]]
- [2ጢሞ2[3]]“እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር ሆነህ፥ አብረኸኝ መከራ ተቀበል።”
- [1ቆሮ9[7]]“ከቶ በገዛ ገንዘቡ በወታደርነት የሚያገለግል ማን ነው? ወይስ ወይን ተክሎ ፍሬውን የማይበላ ማን ነው? ወይስ መንጋ እየጠበቀ ከመንጋው ወተት የማይጠጣ ማን ነው?”
- [ፊል2[25]] “ነገር ግን ወንድሜንና ከእኔ ጋር አብሮ ሠራተኛ ወታደርም የሚሆነውን፥ የእናንተ ግን መልእክተኛ የሆነውና የሚያስፈልገኝን የሚያገለግለውን አፍሮዲጡን እንድልክላችሁ በግድ አስባለሁ”
- [ፊልሞ ቁ2] “ለእኅታችንም ለአፍብያ፥ ከእኛም ጋር አብሮ ወታደር ለሆነ ለአርክጳ፥ በቤትህም ላለች ቤተ ክርስቲያን”
- [ዘጸ15[3]] “እግዚአብሔር ተዋጊ ነው፥ ስሙም እግዚአብሔር ነው”






9ኛ-የምስራቅ በር (East Gate)[ነህ 3²⁹]፡- ተስፋን ያመለክታል። በዚህ መከራ ጭንቀት በበዛበት ዓለም ባለ ሕይወት ሆኖ፥ ዘላለማዊውን ተስፋ መጠባበቅን ያሳያል። የዚህ በር መታደስ እግዚአብሔር ለዘላለም ያዘጋጀልንን ርስትና ሕይወት ለማየት ሁሌም በተስፋ መታደስ እንደሚገባን የሚያሳይ ነው።

[ሮሜ8 18-25]

"ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ። የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃልና። ፍጥረት ለከንቱነት ተገዝቶአልና፥ በተስፋ ስላስገዛው ነው እንጂ በፈቃዱ አይደለም፤ ተስፋውም ፍጥረት ራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነፃነት ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነፃነት እንዲደርስ ነው። ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ መኖሩን እናውቃለንና። እርሱም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን የመንፈስ በኵራት ያለን ራሳችን ደግሞ የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነት እየተጠባበቅን ራሳችን በውስጣችን እንቃትታለን። በተስፋ ድነናልና፤ ነገር ግን ተስፋ የሚደረግበቱ ነገር ቢታይ ተስፋ አይደለም፤ የሚያየውንማ ማን ተስፋ ያደርገዋል? የማናየውን ግን ተስፋ ብናደርገው በትዕግሥት እንጠባበቃለን።"

[ዕብ11]

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።




መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

10ኛ-የሓሚ ፈቃድ/የፍርድ በር (Master Gate) [ነህ3³¹]፡- በኢየሩሳሌም ከተማ ፍርድ የሚሰጥበት ቦታ ነዉ።

† ይኸውም እያንዳንዳችን መንገዳችንን እየመረመርን፥ በራሳችን ፈርደን፥ ከፋውንም አርቀን፥ የእግዚአብሔርን መንገድ መከተላችንን ያሳያል። እግዚአብሔር ሁሌም ትክክል ነውና!!!

[ሰቆ3 40-41]"መንገዳችንን እንመርምርና እንፈትን፥ ወደ እግዚአብሔርም እንመለስ። ልባችንን ከእጆችን ጋር በሰማይ ወዳለው ወደ እግዚአብሔር እናንሣ።"

[1ዮሃ3 19-21]"ልባችንም በእኛ ላይ በሚፈርድበት ሁሉ፥ ከእውነት እንደ ሆንን በዚህ እናውቃለን በፊቱም ልባችንን እናሳርፋለን፥ እግዚአብሔር ከልባችን ይልቅ ታላቅ ነውና ሁሉንም ያውቃል። ወዳጆች ሆይ፥ ልባችንስ ባይፈርድብን በእግዚአብሔር ዘንድ ድፍረት አለን"

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።






የበግ በር፡-የመጀመሪያውም የመጨረሻውም በር![ነህ3[1፤31]]

አሮጌው ሰዋችን ከርሱ ጋር የተሰቀለ ስለሆነ በፀጋ ጉዟችን ላይ የመስቀሉ ሥራ፤ ሁሌም ማዕከላዊ፤ መነሻም መድረሻም መሆኑን ያመለክታል።[1ቆሮ1[23]]



የሰዉ ልጅ ታርክ መቼዉንም ከመስቀሉ ርቆ አላወቀም። አዳምም ወደ መቃብሩ የሄደዉ ይህንኑ ተስፋ ሰንቆ ነዉ። ያ! ይፈስ የነበረዉ የእንስሳት ደም ሁሉ በቀራንዮ አደባባይ ስለ ሰዉ ሁሉ የተሰዋዉን አማናዊ የእግዚአብሔር በግ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያመለክት እንደነበር ዛሬ ለይ ሆነን ስንመለከተዉ፤ የቀደመዉ እዉነት እርሱም አሮጌዉ በር የሰዉ ልጅ ታርክ መነሻዉም መድረሻዉም፤ የመጀመሪያዉም መጀመሪያ፥ እንደሆነ እንገነዘባለን።



እግዚአብሔር በሰዉ ልጅ ለይ ያለዉ ዓላማ ሁሉን በክርስቶስ መጠቅለል መሆኑ እና ለዚሁ ዓለም ሳይፈጠር፥ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ እንደተመረጥን ስንመለከት፤ አሮጌዉ እዉቀት እርሱም የቀደመዉ እዉነት የእግዚአብሔር ልጅ ስለ ሰዉ ዘር ሁሉ መሞት መነሳትም ሆኖ እናያለን።

በርግጥም ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ያለውን የእግዚአብሔርን ሃሳብ ስንመለከተው፥ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሰራው ሥራ በዔድን ገነት ለሰዉ የሰጠዉን የቀደመውንና አሮጌውንም principle በበለጠ ክብር ሲያፀናው ነዉ። በሌላ ቋንቋ እርሱ ባለመለወጥ ሰውን ለውጦ በበለጠ ክብርም አስውቦ ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ወዳሰበዉ እዉነት መልሶናል። በዚህም አሮጌዉ እዉቀት የእግዚአብሔር ልጅ ስለ ሰዉ ዘር ሁሉ መሞቱ መነሳቱም ሆኖ እናገኘዋለን።



# እንግዲህ...ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ማመን ወይም ክርስቶስን መቀበል ማለት በራሱ ምን ማለት ነዉ???





ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን መቀበል ወይም በርሱ ማመን ማለት፤ እግዚአብሔር እዉነት ነዉና አይዋሽም ፤ አስቀድሞ ለሰዉ ልጅ በዔድን ገነት የተናገረዉ ሁሉ እዉነት ነዉ። ከዘመናት በኋላ በስጋ የተገለጠዉ ኢየሱስ፣ የቀደመዉ እዉነትና፤ እዉነተኛ አምላክ ስለሆነ ስለ እዉነት ሊመሰክር መጥቷል፤ እዉነት በእርሱ አለ። እዉነትም እርሱ ነዉ። ብሎ ማመን ነዉ።

[ዮሃ14[6],17[3],17[16] ,18[37]፣ ኤፌ4[21]]



እንግዲህ....

እንግዲህ አሮጌውን በራችንን እናድስ ስንል የቀደመውን የእግዚአብሔርን Principles እንደ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ሃሳብ እንወቃቸው እያልን ነው። ያልነዉ ይህንን ነዉ።

"We have to rest upon old principles of God, these truths will never change."

[R. Stedman]



በነብየ እግዚአብሔር ኢሳያስም እንዲሁ፡

"እኔ አምላክ ነኝና፥ ሌላም የለምና የቀድሞውን የጥንቱን ነገር አስቡ እኔ እግዚአብሔር ነኝ እንደ እኔም ያለ ማንም የለም። በመጀመሪያ መጨረሻውን፥ ከጥንትም ያልተደረገውን እነግራለሁ ምክሬ ትጸናለች ፈቃዴንም ሁሉ እፈጽማለሁ እላለሁ። ከምሥራቅ ነጣቂ ወፍን፥ ከሩቅም አገር ምክሬን የሚያደርገውን ሰው እጠራዋለሁ። ተናግሬአለሁ እፈጽማለሁ አስቤአለሁ አደርግማለሁ።" ይላል።[ኢሳ46 9-11]



ማስገንዘቢያ

† አሮጌውን ቅጥራችን እናድስ ስንል፡-

✓እግዚአብሔር በዔድን ገነት የተናገረው ሁሉ እዉነት ነዉ፤ መነሻችንም ፥ መድረሻችንም እርሱ ነዉ። እያልን ነው።

✓አንድም ፤ የዘፍጥረቱ እግዚአብሔር የተቀረዉ መጽሓፍ ቅዱስ ሁሉ አምላክ ነው። ከዘመን በኋላም በልጁ በኩል የተናገረው ሁሉ እውነት ነው። እያልን ነው።



† ለዚህ ነዉ በዋናነት የትምህርቱ ዓላማ፡

- የቀደመውን የእግዚአብሔርን ጥልቅ ሃሳብ መለስ ብሎ በማየት፤ እግዚአብሔርን እዉነተኛ ፥ ሴይጣንን ዉሸተኛ ለማለት ነዉ ያልነዉ፥
- መዳናችንን በማስረገጥ ፤ የድነትን ጽንሰ ሃሳብ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ለማስረዳት፤ ከተለመደዉ ዓይነትም ወጣ ብሎ የነገረ-ድነት ማጣቀሻ ጽሑፍ ለሚማርም ፥ ለሚያስተምርም ለማቅረብ ነዉ ያልነዉ ፥
- ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በቃል ስለምንሰጠው ምስክርነት ግንዛቤያችንን ለማስፋት ፥ እና
- ከዘፍጥረት 1-3 ያሉትን ዋና ሃሳቦች አጉልቶ በማሳየት ፤የዘፍጥረት መጀመሪያው አምላክ ፤ የተቀረው የመፅሐፍ ቅዱስም ሁሉ አምላክ እንደሆነ በመግለፅ ላይ አነጣጥሯል ያልነዉ ።

† እነዚህን የትምህርቱ ዓላማዎች (ከግንዛቤ በማስገባት)ነው፡

- ቀደም የተረዳነዉን እዉነት ለማጠናከር፥ የረሳነዉን ለማስታወስ፥ የተሳሳትነዉን ለማረም፥ ያላወቅነዉንም ለማሳወቅ የሚሰጥ እንደሆነ ይታወቅልን፥ ስለዚህ ሁላችንም ተማሪዎች ነን ያልነዉ!!!፥

- ትምህርቱ የክርስቶስን ቤተክርስቲያን ልብ ዉስጥ በመያዝ የተዘጋጀ ነዉና፤ ተናጋሪዉንና አነጋገሩን ሳይሆን የሚነገረዉን እዉነት ልክ እንደ ቤሪያ ክርስቲያኖች ከመጽሓፍ ቅዱስ አኳያ በመመዘን ከተቻለ ሁሉንም ፥ ካልሆነ ከፊሉን መቀበል ብልህነት ሲሆን፥ ሁሉንም አለመቀበል ደግሞ የራስ መብት ነዉ ያልነዉ።

...ምን አልባት የማይመለከትዎት ጉዳይ ካለ እባክዎን እርስዎን አይመለከትም ማለት ነዉ!



† አሮጌውን ቅጥራችን እናድስ ስንል የትምህርቱ ይዘት፡

- በስላሴ አስተምሮ ላይ የቆመ ነው፥
- የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነትና የማዳን ስራ በጥልቀት ያያል፥
- በዚሁም፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን መቀበል ወይም በርሱ ማመን ማለት ምን ማለት እንደሆነ አንዱን ሃሳብ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ይመለከታል፥
- ዲኖሚኔሽኖችን አይደግፍም ፥ አይተችምም ፤ ይልቁንም ሐዋሪያዊ ዶክትሪንን ያማከለ ነው፥
- በዚህም አከራካሪ ነጥቦችን ከሰዉ ልጅ ድነት ጋር ከተያያዙ ያለ አድሎ በድፍረት ያቀርባል።

ያልነዉ በዚህ የተነሳ ነዉ።



መጽሓፍ ቅዱስ፡-

“ቅጥር እንደሌላት እንደ ፈረሰች ከተማ፥ መንፈሱን የማይከለክል ሰው እንዲሁ ነው።”ምሳ25[28]

“ጉድጓድን የሚምስ ይወድቅበታል፥ ቅጥርንም የሚያፈርስን እባብ ትነድፈዋለች።”[መክ10[8]]



በዚህም ለእግዚአብሔር ያለዉን ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ማንም አያውቅምና፤ በፊቱ መቆም እንደማይገባን አምነን ፥ በተዋረደ ልብ በመሆን ፤ ከቀደምት አበዉ የተማርነዉንና እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል የገለጠልንን እዉነት ፤ መንፈሳዊን ነገር ከመንፈሳዊው ጋር አስተያይተን፥ እግዚአብሔር አስቀድሞ ከዘመናት በፊት ለክብራችን የወሰነውን፥ ተሰውሮም የነበረውን የእግዚአብሔርን ጥበብ በምሥጢር እንናገራለን።

ይትባረክ እግዚአብሔር፣

አምላከ አበዊነ።

የአባቶቻችን አምላክ፣

እግዚአብሔር ይመስገን።

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።